
# ምዕራፍ አንድ

## የምልክት ቋንቋ ምልዑነት




ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣

- ከምልክት ቋንቋ ጋር የተያያዙ ምልክቶች እውቀታችሁን ታዳብራላችሁ፣
- በምልክት ቋንቋ ለመግባባት ወሳኝ የሆኑ ነጥቦችን በኢምቋ ታስረዳላችሁ፣
- ከምንባቡ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን ትለያላችሁ፣
- ከቁልፍ ምልክቶች ውስጥ በአንዱ እሴት ብቻ የሚለያዩትን ታሳያላችሁ፣
- የኢምቋ ዐረፍተ ነገር ትሰራላችሁ፣
- ስርዓት ጠብቃችሁ ትወያያላችሁ።

## ቁልፍ ምልክቶች



ምልክት ቋንቋ



የእጅ ቅርፅ



የመዳፍ አቅጣጫ




ምላስ




የእጅ እንቅስቃሴ




ድግግሞሽ




እጅ የሚያርፍበት ቦታ



በእጅ የማይገለጹ እንቅስቃሴዎች




ከንፈር



መዘርጋት




ወደ ቀኝ



ድምጽ



መታጠፍ




መቆለፍ



ጥርስ




ወደ ውጭ




ወደ ውስጥ




ፊትለፊት




ወደታች




ወደላይ



ወደግራ



ሃይል




የፊት እንቅስቃሴ

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## እይታዊ ንባብ






### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. ከላይ የተቀመጡትን ሥዕሎች በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ፡፡
2. በስዕሎቹ ላይ የተመለከቱትን ነገሮች ልንጠቀምባቸው የምንችለው እንዴት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ በኢምቋ ያቀርቡላችኃል፡፡ መምህራችሁን በትኩረት ተከታትላችሁ ለጥያቄዎች በኢምቋ መልስ ስጡ፡፡

1. ምልክት ቋንቋ ከንግግር ቋንቋ የሚለየው በምንድን ነው?
2. ምልክት ቋንቋ የተሟላ ቋንቋ መሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ምንባብ

ተማሪዎች፤ መምህራችሁ የምልክት ቋንቋ ምልዑነት የሚለውን ምንባብ ሲያቀርቡላችሁ ሐሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን፣ የኢምቋ አጠቃቀማቸውን በጥንቃቄ ተመልከቱ።

### የምልክት ቋንቋ ምልዑነት

ምልክት ቋንቋ እንደማንኛውም ቋንቋ ራሱን የቻለ ቋንቋ ነው። ማንኛውም ቋንቋ ትርጉም ሊኖረውና ለዕርስ በርስ መግባቢያነት ሊያገለግል የሚችለው፣ ስርዓት ሲኖረውና ተጠቃሚዎችም ይህን ስርዓት በትክክል ሲከተሉ ብቻ ነው። በንግግር ቋንቋ ውስጥ ከእነዚህ ስርዓቶች አንዱ ስርዓተ ድምፅ ነው። የከንፈር፣ የምላስ፣ የጥርስ፣ የድድ፣ የላንቃ፣ የትናጋ፣ ወዘተ፣ እንቅስቃሴዎችን ስርዓት ባለው መንገድ በመለዋወጥና በማቀናጀት የተለያዩ የቋንቋ አሐዶች ይፈጠራሉ። የምልክት ቋንቋም የራሱ የሆነ የ"ድምፅ አወጣጥ" ሥርዓት አለው። ሥርዓቱ የሚገለፀው ግን በድምጽ ሳይሆን በእጅ ነው። የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋን ጨምሮ ሁሉም የምልክት ቋንቋዎች፣ ከሚከተሉት አምስት መሰረታዊ ክፍሎች የተገነቡ ናቸው።

የመጀመሪያው ክፍል የእጅ ቅርጽ የሚባለው ነው። ይህም ምልክቱ በሚሰራበት ጊዜ በእጅና በጣቶች ላይ የሚታየው የመዘርጋት፣ የመተጣጠፍ፣ የመቆለፍ፣ ወዘተ፣ ሂደት የሚፈጥረው ቅርጽ ነው። ይህም ቅርጽ ለምልክቶቹ ትርጉም ይሰጣል።

ሁለተኛው ክፍል የመዳፍ አቅጣጫ ነው። ይህ ማለት ምልክቶቹ በሚሰሩበት ጊዜ መዳፍ የሚያመላክተው አቅጣጫ ነው። ምልክቶች በሚሰሩበት ጊዜ መዳፍ ወደ ሰባት መሰረታዊ አቅጣጫዎች ያመላክታል። እነሱም ወደ ውጭ፣ ወደ ውስጥ፣ ወደ ታች፣ ወደ ላይ፣ ወደ ቀኝ፣ ወደ ግራና እርስ በርሱ የመተያየት ናቸው። የመዳፍ አቅጣጫ መለወጥ ለምልክቶቹ ትርጉምና ልዩነት ይሰጣል።

ሦስተኛው ክፍል የእጅ እንቅስቃሴ ነው። ይህም ሲባል ምልክቶቹ በሚሰሩበት ጊዜ እጆች የሚያደርጉትን ስርዓት የያዘ እንቅስቃሴ ነው። ይህ እንቅስቃሴም ለምልክቱ ትርጉም ይሰጣል። ምልክቶች በሚሰሩበት ወቅት እጆች ወደ አካል ሊመጡ ወይም ከአካል ሊርቁ፣ ወደ ታች ወይም ወደ ላይ ወይም ወደ ሌላ ወደተፈለገው አቅጣጫ ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ። የእጆች እንቅስቃሴ ዓይነት፣ አቅጣጫ፣ ድግግሞሽ፣ ሃይልና መጠን አለው። የእነዚህም መለዋወጥ የትርጉም ለውጥ ይፈጥራል።

አራተኛው ክፍል እጅ የሚያርፍበት ቦታ ነው። ምልክቶች በሚሰሩበት ጊዜ እጆች መነሻና መድረሻ እንዲሁም አቅጣጫ አላቸው። እነዚህ መለዋወጥም የትርጉም ለውጥ ይፈጥራል። እጅ የሚያርፍበትን ቦታ ለመናገር የሚታየው የእጅ ቅርጽ፣ ከተናጋሪና ፊት ለፊት ካለው ባዶ ቦታ (አየር) ውስጥ ተነስቶ ያረፈበት የአካል ክፍል ነው።

የመጨረሻው ክፍል በእጅ የማይገለጹ እንቅስቃሴዎች የሚባለው ነው። ከላይ የተገለጹት

አራት የምልክት ቋንቋ ምልክቶች መሰረታዊ ክፍሎች ውስጥ የማይካተቱ ነገር ግን የሁሉም አካል የሆኑና ለምልክቶች ትርጉም የሚሰጡ ብዙ የጥያቄ፣ የስሜት፣ ወዘተ፣ መግለጫዎች የሆኑ የፊትና የአካል እንቅስቃሴዎች አሉ:: እነዚህ ክፍሎች በምልክት ቋንቋ አጠቃቀም ወቅት አንድ ሰው የሚናገራቸውን ምልክቶችት በመጎተት፣ በማርዘም፣ በዝግታ ወይም በፍጥነት በማወጣት፣ በመጮህ፣ ለስለስ ባለ ሁኔታ በመናገር፣... የሚፈጥረው ዓይነት ያመጣሉ::

*ምንጭ:- ጳወሎስ፣ 2007 የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ ማስተማሪያ መመሪያ፣ (ተሻሽሎ የቀረበ)*

## መልመጃ አንድ:-

### አይቶ መረዳት

የሚከተሉት ጥያቄዎች በዋናነት በምንባቡ ውስጥ የተማራችኋቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶችና ዐረፍተ ነገሮች አጠቃቀም ግንዛቤያችሁን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ::

1. ከምንባቡ ውስጥ የወደዳችሁትን አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ መምህሩ ባቀረቡበት መንገድ በክፍል ውስጥ በኢምቋ አንብቡ::
2. የምንባቡ ዋና ዋና ነጥቦች ጥቀሱ::
3. የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳችሁ አገላለጽ አስረዱ::

## መልመጃ ሁለት:-

### የማስታወስ ችሎታ

የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ::

1. በምንባቡ መሰረት ቋንቋ ለዕርስ በርስ መግባቢያነት ሊያገለግል የሚችለው ምን ሲሆን ነው?
2. ምልክት ቋንቋ ከንግግር ቋንቋ የሚለየው በምንድን ነው?
3. በምልክት ቋንቋ ስርዓት መሰረት የእጅ ቅርጽ የሚሰራው እንዴት ነው?
4. በምልክት ቋንቋ ስርዓት መሰረት የመዳፍ አቅጣጫ የሚሰራው እንዴት ነው?

5. በምልክት ቋንቋ ስርዓት መሰረት የእጅ እንቅስቃሴ የሚሰራው እንዴት ነው?
6. በምልክት ቋንቋ ስርዓት መሰረት እጅ የሚያርፍባቸው ቦታዎች ምን ምን ናቸው?
7. በምልክት ቋንቋ ስርዓት መሰረት በእጅ የማይገለጹ እንቅስቃሴዎች የምናሳይባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው?

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### የቡድን ስራ

#### መልመጃ አንድ:-

**በቡድን መስራት**

መምህራችሁ በቡድን ይከፋፍሏችኋል:: በቡድን ከተከፋፈላችሁ በኋላ የአምስቱ መሰረታዊ የምልክት ቋንቋ ክፍሎች በተወሰኑ ምልክቶች ላይ መለዋወጥ በትርጉም ላይ ለውጥ እንደሚያመጣ ተወያዩ:: የውይይታችሁን ውጤት በቡድናችሁ ተወካይ በኩል ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢምቋ አቅርቡ::

#### መልመጃ ሁለት:-

**ዐረፍተ ነገር ምስራታ**

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው::በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች በመጠቀም የራሳችሁን የኢምቋ ዐረፍተነገር ስሩ::

1. ቋንቋ
2. ምልክት ቋንቋ
3. ከንፈር
4. ጥርስ
5. ምላስ
6. እጅ
7. መዳፍ

8. ቦታ
9. እንቅስቃሴ
10. አቅጣጫ
11. ቅርጽ
12. ፊት

## መልመጃ ሦስት፡-

### የሚመሳሰሉትን እሴቶች መለየት

የሚከተሉት ትይዩ ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው። በትይዩ ቃላት የተወከሉት ምልክቶች በአንዱ እሴት ብቻ የሚለያዩ ናቸው። የሚለያዩበትን እሴት በክፍል ውስጥ ዓሣዩ።

ምሳሌ አንድ፡-

መብላት- መጠጣት

መልስ፡- በእጅ ቅርጽ ይለያያሉ

ምሳሌ ሁለት፡-

አባት- እናት

መልስ፡- በቦታ ይለያያሉ

ምሳሌ ሦስት

ት/ቤት- ወረቀት

መልስ፡- በእንቅስቃሴ ይለያያሉ

ምሳሌ አራት፡-

ስም - መቀመጥ

መልስ፡- በመዳፍ አቅጣጫ ይለያያሉ

1. ቡና - ስራ
2. ማግባት- መፍታት
3. አበባ- መሳም (ለሰላምታ)

4. ቅናት- መራራ
5. ይቅርታ- ንጹሕ
6. ድብርት - እንኳን
7. ቀልድ - አይጥ
8. ጥሩ - መጥፎ
9. በጋ- ደረቅ
10. ጤና - ሰላምታ
11. ባቡር - አጭር (ለነገር)
12. ስም - አጭር (ለነገር)

## ክፍለ ትምህርት አራት

### የምልክቶች ትንታኔ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማራችኋቸውን ዋና ዋና ምልክቶች ትንተና በክፍል ውስጥ ዓሣዩ።

ምሳሌ፡- ጥርስ

1. እጅ ቅርጽ፡- አመልካች ጣት
2. የእጅ ቅርጽ የሚያርፍበት ቦታ፡- በጥርስ ላይ
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡- ወደ ሰውነት
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡- ከሰውነት ወደ ጥርስ አቅጣጫ
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎ፡- ፊታ ያለ ፊት